ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

Tel 202291 4217 mailling address: P.O.Box 73337, Washington Dc 20011

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በጥር 25, 2009 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# ውይይትና ድርድር ለምን ዓላማ ?

ተጋብቶ መፋታት፤ ተለያይቶ መታረቅ፤ ተላቅሶ መሳሳቅ ፤ ተጋድሎ ደም ማድረቅ፤ ከዚያ በኋላ ግን፤ ሁሉንም ጥብ - ርግፍ አድርጎ ፤ በአዲስ መንፈስ ፤ አዲስ ሕይወት መኖር ፤ በኢትዮጵያ ባኅል ያልተለመደ አልነበረም ። የተጣላው ሁሉ ፤ ዕርቀ-ሠላም አውርዶ በሠላም አብሮ ከመኖር የተሻለ ሌላ ምርጫ አለመኖሩን ስለሚያውቅ፤ ሕዝብ ይኸንን ምርጫ ያከብረዋል ። አሁንም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ፤ በዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ ህያው ሆኖ ይኖራል ። በተግባር ይውላል ። ይኽ ማኅበራዊ ህይወት ሚዛን የደፋ ፤ ሕዝባዊ መስተጋበር ሆኖ ለዘመናት ኖሯል ። ሕዝቡ ሲተዳደርበት ቆይቷል ። የገዥዎች አዋጅ፤ የዳኞች አማላጅ፤ ያጥቢያ ዳኛ ግልምጫ፤ የፖሊሶች ርግጫ ባልስፈለገበት ዘመን ፤ ሕህብረተሰቡ፤ ተቀያይሞ እየታረቀ፤ ተበዳድሎ እየተካካሰ፤ በአብሮነት ኖሯል ።

በነፃነት የኖረ ሕዝብ፤ ከፈጣሪውና ከኅሌናው በቀር ማንንም የሚፈራ አልነበረም ። ያለ ፍርሃትና ስጋት በነፃነት የኖረው ሕዝብ ደግሞ፤ በግል ሕይወቱ የማንንም ጣልቃገብነት አይፈልግም ። ለነፃናቱ ቀናዒ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በግል ሕይወቱ፤ በትዳሩ -በጎጆው - በሃይማኖቱ -በሀገሩ- በድምበሩ- ባድባሩ- ባውጋሩ፤ የሚተናኮለውን አጥብቆ የቃወማል ። እስከ ሕይወት መሥዋዕት ድረስ ይጋተረዋል !

በማኅባራዊ ኀይወት ውስጥ ነዋሪዎቹ እንዳይስማሙ የሚያደርጓቸው ልዩ ልዩ መንስዔዎች ቢኖሩም፤ ታርቀው በሠላም ለመኖር የሚያስችላቸው የተለያዩ የመስታረቂያ ዘዴዎችና ብልሃቶች ደግሞ አሏቸው። ምን ጊዜም ቢሆን፤ በህዝብ መካከል፤ ቋሚም ሆነ መሠረታዊ ጠላትነት የለም ። በዚህ ምክንያት፤ ለማንም አልኩ-ኩባይ - ሠላም አድፍራሽና አፈቀላጤ - አዛኝ -ቅቤ-አንጓች ፤ ተልመጥማጭና አቁላቢ በሩን ሳይከፍት፤ የተቀያየመው እየታረቀ ሠላማዊ ህይወቱን በአብሮነት ይቀጥላል ።

ከሰማንያ በላይ ብሄር- ብሄረስብ ያላት ሀገር ፤ የዜጎቿ የአብሮ መኖር ዓብነቱ፤ ብልሃቱና ምሥጢሩ ይኸ ነው ። ይኸንን ሀገራዊ ፀጋ ነው ዛሬ፤ ከፋፋይ ዘረኞች ሊያጠፉት የሚከጅሉት ። ከፋፋዮች ፤ ደርቀው ይቀሯታል እንጅ፤ ዓላማቸው አይሳካም ። ሀገሪቱም እንደገና ታብባለች ፤ ዜጎቿም በሠላም አብረው መኖራቸውን ይቀጥላሉ ። ይኽ ደግሞ፤ የባዶ ተስፋ ምኞት አይደለም ። ሀገራችን አንድነቷን ጠብቃ እንደምትቀጥል ሕዝቦቿ በዕርገጠኝነት ያምናሉ ። ደምና ዕምባ በተቀላቀልበት ቀለም የተጻፈ ታሪካቸው ይመሰክረዋል ።

ሀገራዊ ችግር የሚፈጠረው፤ በሕዝብ ሠላማዊ ህይወትና ኑሮ ውስጥ የመንግሥት ጣልቃ -ገብነት ሲደነቆር ነው። በተለይ ደግሞ፤ ከፋፋይና አምባገነናዊ ድርጅት፤ ያለ ሕዝብ በጎ ፈቃድና ይሁንታ፤ ሥልጣን ከጨበጠ፤ በቁጥጥሩ ስር ያደረገው ህዝብ ተባብሮ፤ ተስማምቶ በሠላም አንድ ላይ እንዲኖር አይፈልግም ። ሕዝብ ከተስማማ ፤ የእርሱ እህል -ውሃ እንደሚቆረጥ ፤ አምባገነን አገዛዝ አበክሮ ይረዳል ። ስለሆነም፤ የሕዝቡን ሠላም ለመበከል፤ ለማደፍረስ የማያደርገው ጥረት አይኖርም ። ይኸ ጠረቱ እያለተሳካ መሄዱን ከተገነዘበ፤ የተስፋ መቁረጥና የሚይዘው -የሚጨብጠው እስከማጣት ወደሚያዘነብልበት ደርጃ ይደርሳል ። ከዚያ በኋላማ የአዕምሮ ረሃብተኛ ሆኖ መቅረት ነው። በርሃብተኛ አዕምሮ የሚንከላወስ አካል፤ በሞትና ሽረት መካከል በመሆን፤ የሚይዘው -የሚጨብጠው ያጣና ያገኘውን ሁሉ እንደ አበደ ውሻ መልከፉን ይቀጥላል። የገነባው አጥርና ምሽግም ጊዜውን እየጠበቀ ይፈርሳል። ጭንቅላቱ፤ በጭንቀት የተዋጠ በድን ከመሆን አያልፍም።

የደነገገው አቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ ፋይዳ ቢስ መሆኑን ሲረዳ፤ ለዕድሜው ማስረዘሚያ የሚጠቅመው እየመሰለው፤ ዕርቅና ሠላም ይምጣልኝ ብሎ ያስወራል ። ኑ እንነጋገር ፤ እንወያይ፤ ለሠላምና ለእርቅ በር ከፍቻለሁ ፤ ይላል ። ይህንን ባለበት አፉ ደግሞ፤ " ከእኔ ደጋፊዎች በስተቀር ወደ ስብሰባው አዳራሽ መጠጋት ክልክል ነው ! " የሚል ማስታዎቂያ ለጥፎ ፤ በቢጫ ፕላስቲክ ሪባን አጥር ተክብቦ ይቀመጣል ።

የሰሞኑ ፤ ከወያኔ ጋር የዕርቅና ሠላም ውይይትን አስመልክቶ በየቦታው የተለያዩ ውዥንብሮች፤ ውቂው- ደብልቂውና ትርኪ-ምርኪዎች ፤ ከአንዳንድ አካባቢዎች ይሰማሉ ። በወያኔ በኩል የሚነፍሰው ይኸ አቅጣጫ አስለዋጭና ትጥቅ አስፈች ፕሮፓጋንዳ፤ ያገዛዙን ጊዜ ለተወሰኑም ቀናት ቢሆን ለማሰረዘሚያ ከሚደረግ ጥረት አያልፍም። ወያኔ ይኸንን ቢያደርግ አያስደንቅም። ለአርሱ፤ የሞት -ሽረት ጉዳይ ነውና ! በሥልጣን ቆይቶ መዘርፍ ወይም ከሥልጣን ተባርሮ ቀልጦ መቅረት ነው። ወያኔ ደግሞ ሰማይ ዝቅ መሬት ከፍ ቢል፤ በሠላም ሆነ በፈቃዱ ከሥልጣኑ የሚወርድ ቡድን አይደለም ። ከየትስ የተማረው?

ከርሱ በፊት የነበሩት ሁሉት አጋዛዞች መጨረሻቸው ምንና እንዴትስ ነበር ? ከሥልጣናቸው የተወገዱት? ወድደው ነው ? ወይስ ተግድደው? በፀጋና በኩራት ነው የሄዱት ? ወይስ በውርደትና በሃፍረት ነው የተባረሩት ? ታዲያ ወያኔን አሁን ምን አስገዳጅ ሁኔታ አጋጥሞት ነው፤ በሠላምና በዕርቅ መንግሥታዊ ሥላጣኑን የሚጋራው ?

በኢትዮጵያ የወርቅ ማዕደን፤ ያላአንዳች ተቀናቃኝ እንደልቡ ተንሰራፍቶ ተቀመጦ የሚበዘብዝ ቡድን ፤ እንዴትስ አድርጎ በፈቃዱ ሥልጣኑን ያካፍላል ተብሎ ይጠበቃል ? ይታሰባል ? የትኛውን ተቃዋሚ ኃይል ሰግቶ ነው፤ መጥታችሁ ለዕርቅ እንደራደር ብሎ ከልቡ የሚያስበው ? ወይስ የእርሱ ሙሉ ተባባሪዎች፤ የሥልጣን አጎብዳቢዎችንና የጥቅም አጋሮቹን ብቻ መርጦ በማነጋገር ፤ በኢትዮጵያ ዘላቂ ሠላምና መረጋጋት ይመጣል ተብሎ በህልም ቅዠት ለመባነን ነው ? ሕልም አይከለከልምና የሚያልመው ሁሉ ምናልባት፤ በእርጎ ባኅር ለመዋኘት ከፈለገ ፤ ይግባና ይሞክረው ።

ይህን ምኞት ለማሳካት ካልሆነ በስትቀር ፤ አሁን ወይኔን፤ ወደ ክብ ጠረጴዛ እንዲመጣ የሚያስገድደው ሁኔታ አለ ለማለት የሚቻል አይደልም ቢባል፤ ከዕውነት የራቀ ሊሆን አይችልም። አሁን በሕዝቡ አመፅ አከርካሪ አጥንቱ እያተንኮታኮተ በመሄድ ላይ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ ጭንቅላቱ አሁንም እየተልሞሰሞሰ ያለ ቡድን ነው። ይኸ ታልሞስሟሽ

ጭንቅላቱ ፤ አሁንም ህዝቡን ለመግዛት፤ጉልበቱም ፤ ኃይሉም አለኝ ብሎ ራሱን እንዲያታልል አድርጎታል ። በመሬት ላይ የሚታየው የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ የሚገልጸው ግን ተቃራኒውን ነው ፡፡ ሥርዓቱ " አልሞትኩም ብየ አልውሽም " ለማለት ባይደፍርም፤ ወደ ከርሰ ማቃብሩ እያዘገመ እንደሆነ ግን ደጋፊዎቹና ጋሻ ጃግሬዎቹ ሳይነግሩት አልቀሩም ። " እባክህ መውጫ-ቀዳዳ ፈልግና እኛንም ፤ ከሕዝብ አመፅ እሳተ- ገሞራ አውጣን እያሉ መማፀናቸው ፤ ያደባባይ ምሥስጥር ከሆነ ቆይቷል ። ምዕራብያኑም፤ የሀገሪቱን ውስጠ- ምሥጥር ፤ ጓዳዋን ሁሉ ሳይቀር በሚገባ ስለሚያውቁ፤ ኢትዮጵያ ወዴት አቅጣጫ እያመራች እንደሆነ አይጠፋቸውም ። ሕዝባዊው አመፅ ሲፋፋም ፤ እንደ ቀድሞው የግብፁ መሪ ሁስኒ ሙባረኽ አይከዱ ክህደት እንደሚከዱት የተወቀ ነው ። ወያኔም ይኽንን አያውቅም ማለት አይደለም ። ይኽን በመጠርጠሩም፤ ጊዜው እየመሸበት ፤ እህል -ውሃው እያከተመበት መጣቱን አልተረዳም ማለት አይደለም ፡፡የመልቲነት ባኅርዩ ይኽንን ለመረዳት ያስችለዋል ። ከዚህ ግንዛቤ በመነሳት ፤ የአደጋ መከላከያ ዘዴውን ከማድረግ የሚቆጠብ አይሆንም ። ወያኔ ማነኛውንም ከስተትና ገጠመኝ እንዲሁ በዕዝኅላልነት የሚያልፍ ቡድን አይደለም ። የትኛውንም ዕድልና አጋጣሚ በችልታ ያልፋል ተብሎ አይጠበቅም ። " የሉኝታ የራስ አሊን ቤት የፈታ " የሚለውን ብሂል በአግባቡ የሚጠቀም መሰሪ ስብስብ /ጉጇሌ ነው፤ ወያኔ ። በኢትዮጵያውያን ሥነ ልቦናዊ-[ዕምነት- መስተጋበር ፤ እያሾፈ ለመጠቀም ይሞከራል እንጅ ፤ የሕዝቡን ዕምነትና ባኅል የሚያከበር ስብስብ አይደለም ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አኩሪ ባኅልና ልምድ ብቻም ሳይሆን ፤የሰውን ልጅ ከእንሥሣት የሚለያቸው ባኅርያት ፤እንደ ይሉኝታ- አዞሮ መመልከት- የኅሊና ፍርድ- መርኅ -የገቡትን ቃል ማክበር - ለዕምነት ተግዥነት- ለሌላ ማሰብ/ማዘን- ለመጭው ትውልድ መጨነቅ - ከታሪክና ትውልድ ወቀሳ ነፃ ለመሆን ማሰብ- የመሳሰሉት ሁሉ ወያኔዎቹን አያስጨንቃቸውም ። እንዲያውም ፤ በአንፃሩ፤ እነኝህን ሁሉ ማፌዥያዎች አድርገዋቸዋል ። ። ትኅትናን እንደሞኝነት፤ ትዕግስትን እንደ ፍረሃት ፤ ይሉኝታን እንደ ቂልነት ፤ አርቆ ማሰብን እንደ ፖለቲካ ፋራነት እየተቆጠረበት ፤ ሕዝባችን እስካሁን ብዙ ተበድሏል ።

የሰሞኑ፤ ለዕርቅና ሠላም ድርድር ጮኸትና ሁካታ፤ በወያኔ በኩል እንዲናፈስ የተደረገው፤ በሁለት ድልዳሎች ላይ አፈራግጦ ከመቆም የመጣ ፤ የጊዜ መግዣ ሽወዳ ነው ።

**አንደኛው ፡---** ከዕለት ወደ ዕለት ግለቱና ገሞራው እያጨመረ የመጣውን ሕዝባዊ አመፅ ውሃ ለመቸለስ የታሰበ ሙከራ እንደሆነ ይገመታል። በተለየ፤ የኦሮሞውና የአማራው የትግል ህብረት እያየለ ከመምጣቱ በፊት፤ ኃይሉን ለማኮላሸት ከሚል ዕሳቢ የመጣ ነው ብለው ብዙዎቹ ያምናሉ ። የወጣቱ ትውልድ አልገዛም ባይነት የሚያስከትለውን አባሳ፤ የወያኔ መሪዎች ከማንም በበለጠ ያውቁታል ።የወጣት አመጽና ትግል ደግሞ የሚያመጣውን ውጤት የሚያውቅ ያውቀዋል። ይኽ የወያኔ " ኑ እንታረቅ ጥሪ "፤ ሳልቀደም ልቅደም እርምጃ ከመሆን አያልፍም ።

**ሁለተኛው ፡ የወያኔ መሪዎች** ሕዝቡን ለሀገሩ ያለውን ጭንቀትና ጥበት ለራሳቸው ፖለቲካ ትርፍ ሊጠቀሙበት የሚያደርጉት ብልጣ ብልጥነት ነው። “ ሀገሪቱ መስቀለኛ መድገድ ላይ ነች። ለመከፋፋል- ለመበታተን ከመጨረሻው ጠርዝ ላይ ትገኛለች። እባካችሁ አንድ ነገር እናደርግና ሀገሪቱን እናድናት” በማለት ለመጻደቅ መሆኑ ግልጽ ነው።

የሚገርመው ግን ይህን የወያኔን መሰሪ ተንኮል ተቀብሎ በፈለገው መንገድ ቢሆንም ከወያኔ ጋር ተወያይቶ ሰላምና እርቅ እናምጣ የሚሉት ክፍሎች እንቅስቃሴ ነው። ይኽንን ሙዚቃ በማሰማት ለወያኔ አገዛዝ አዲስ ትንፋሽ እየፈጠሩለት

ይገኛሉ። **ይህ ሙዚቃ ዞሮ ዞሮ** ዘረኛውን አጋዛዝ ትንሽ ቅብዐ፤ ሜሮን አርከፍክፎ ፤ አዳፋ ልብሶን በመቀየር ፤እንዲታየይ ከማድረግ ያለፈ ፋይዳ አያመጣም ። ሊያስከትል የሚችለው ውጤት የተቃውሞውን ጎራ የበለጠ ከፋፍሎና እርስ በርሱ እንዲራኮት አድርጎ ትግሉን ማዳከም ይሆናል። ትግል የሰላቸውና ተስፋ የቆረጠው ሁሉ ፤ ምክንያት ያገኘ እየመሰለው ፤ በአገዛዙ ማዕቀፍ ውስጥ ለመግባት ራሱን ያመቻቻል ። " የቀረችኝን ዕድሜ በሠላም አርፌ ልረፍ " ለሚለውና ወኔ ለሰለበው ግለሰብ፤ ከቅብዝብዝ ጎሊና " ነፃ " የወጣ ስለሚመስለው፤ " እየተገዙ መታገል ይሻለኛል " ብሎ ይገባል ። ገብቶ የሚያጋጥመው ግን ፤ እያተገዙ መታገል ሳይሆን፤ እያታሹ መደቆስ ነው ። አስገብቶ ማሸት፤ የወያኔ የአገዛዝ ስልት በመሆኑ፤ " ከመጣሽ ማርያም ታምጣሽ " በማለት ፤ የመጣላቸውን ሁሉ አሽከርና አገልጋይ በማድረግ በንቀትና በሽሙጥ ከመግዛት ወደ ኋላ አይሉም።

ወኔ ያጡ የተቃዋሚ ክፍሎች ወያኔ ባጠመደው የተኮል ወጥመድ ውስጥ መዘፈቃቸው የሕዝብ ወገንና ለሕዝብ የሚታገሉትን የተቃዋሚ ክፍሎች ሊያጠናክር እንደሚችል ማረጋገጥ ይችላል። የትግሉን ስልት፤ ከተዘበራረቀ ዕይታ ነፃ ሊያወጣው ይችል ይሆናል ። ይኸ ማለት፤ ወያኔ ተወግዶ አዲስ የሥርዓት ለውጥ መምጣት ግድ ነው የሚለው ክፍል ፤ ያንበሳውን ድርሻና ኃይል እየያዘና እያረጋገጠ፤ ትግሉን በማስተባበር ፤ ዓላማውን ግብ ለማድረስ በርትቶ እንዳንይሰራ የሚያድርጉትን ዕንቅፋቶች እያስወገደ ትግሉን ይቀጥላል። የጠራ ዓላማ ፤ የተስተካከለ የትግል ሜዳ፤ አይበገሬ ታጋዮች እንደ አሸን- ከታብ የሚፈለፈሉበት መልካም አጋጣሚ ይፈጠራል ። (" ውሾቹ መጮኻቸው፤ ግመሎቹም እንዳሻቸው መራመዳቸው " እየቀረ፤ ) አንበሶቹ እየተጣደፉ ዓላማቸውን ለማሳካት ፤ የሚረባሩበበት ወቅት ማየት ሩቅ አይሆንም ።

ይኸ ሁኔታ በሚከሰትበት ወቅት፤ ወያኔና ምዕራባውያን አለቆቹ፤ ቆሎ በሚያጎራርስ ፍቅር መሆናቸው እያከተመ፤ ዐይንህን ላፈር ፤ የሚባባሉበት ወቅት መምጣቱ አይቀሬ ነው። ብዚያን ጊዜ፤ ጥሎ በመፈርጠጥና መክቶ / ቆርጦ በመዋጋት መካከል ያለውን ልዩነት ለማየት ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕድል ይኖረዋል ። ሁሉም ዜጋ፤ ለዕድሜው ዕድሜ ይስጠው !

ከዚህ በተረፈ የውይይትና የድርድር ሀሳብ ሊነሳ የሚችለው በሥልጣን ላይ ያለው አምባገነን ኃይል በሕዝብ የበላይነትና የሥልጣን ምንጭነት አምኖ ሥልጣኑን ለሕዝብ ለማስረከብ ዝግጁ ሆኖ ሲገኝና ይህንንም በተግባር ሲፈጽም ነው። የሕዝብ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች አለገደብ መከበር፤ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች አለምንም ቅደመ ሁኔታ መፈታት፤ ገደብ የለሽ የፕሬስ ነጻነት መኖር ለውይይቱም ሆነ ለድርድሩ ቅድመ ሁኔታዎች ሲሆኑ የኢትዮጵያ አገራዊ አንድነትና የሕዝቡ እኩልነትና ነጻነት ለድርድር የሚቀርቡ አይሆንም።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !